ድሃ ማን እንደሆነ ታውቃላችሁን?

ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "ድሃ ማን እንደሆነ ታውቃላችሁን?" ሶሐቦችም: "እኛ ዘንድ ድሃ ማለት ዲርሀምና
መጠቃቀሚያ እቃ የሌለው ሰው ነው።" አሉ። እርሳቸውም: "በኡመቴ ውስጥ ድሃ ማለት የትንሳኤ ቀን ሶላት፣ ፆም፣ ዘካ ይዞ የሚመጣ ነው። ነገር ግን ሲመጣ ይህንን ሰድቧል፣ ይህንን በዝሙት ዘልፏል፣ የዚህን ገንዘብ በልቷል፣ የዚህን ደም አፍስሷል፣ ይህንን መትቷል። ለዚህኛውም (ለተበዳዩ) ከመልካም ስራው ይሰጠዋል። ለዚያኛውም ከመልካም ስራው ይሰጠዋል። በርሱ ላይ ያለበት ሀቅ ተፈርዶ
ሳይጠናቀቅ መልካም ስራው ካለቀ ደሞ ከነርሱ ወንጀል እየተወሰደ በርሱ ላይ ይጫንበትና ከዚያም እሳት ውስጥ ይጣላል።" አሉ።
[ሶሒሕ ነው።] [ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ባልደረቦቻቸውን: ድሀ ማን እንደሆነ ታውቃላችሁን? ብለው ጠየቁ። እነርሱም: በመካከላችን ድሃ የምንለው ገንዘብና እቃ የሌለውን ነው አሉ። እርሳቸውም: በኡመቴ ውስጥ የትንሳኤ ቀን ድሃ የሚባለው እንደ ሶላት፣ ዘካና ፆም የመሰሉ መልካም ስራዎችን ይዞ የሚመጣ ነው። (ነገር ግን) ሲመጣም ይህንን ሰድቦታል፣ ይህንን በክብሩ ዘልፎታል፣ የዚህን ገንዘብ በልቶ ክዶታል፣ የዚህን ደም አፍስሶ በድሎታል፣ ይህንን ደግሞ ደብድቦ አዋርዶታል። ለተበዳዮቹም ከምንዳዎቹ እየተቀነሰ ይሰጣቸዋል። እርሱ ላይ ያሉት ሐቆችና በደሎች ተፈርዶ ሳይጠናቀቅ መልካም ስራው ከተጠናቀቀ ከተበዳዩ ወንጀል ይወሰድና ወደ በዳዩ መዝገብ ይደረጋል። ከዚያም ምንም መልካም ስራ ስላልቀረው እሳት ውስጥ ተወርውሮ ይጣላል።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/6454